ማህበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ)
Forum for Social Studies (FSS)
የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች

ቁጥር 1

# የአካባቢ ጥበቃ

የመንግስት ህግና ፓሊሲ አውጪዎች፤ ምሁራንና ፓለቲከኞች ድርቅ፣ ረሀብና የተፈጥሮ መዛባት ድንገተኛ ደራሽ ችግሮች ሳይሆኑ የረጅም ጊዜያት ውጤት መሆናቸውን ጠንቅቀው ያውቃሉ። የተፈጥሮ መዛባት፣ ድርቅና ረሀብ በተፈጥሮ አካባቢ ላይ በደረሰ የደን መጨፍጨፍ፣ የአፈር መሸርሸር፣ የአየርና የውሀ መበከል እንዲሁም የብዝሀ-ህይወት(Biodiversity) መጥፋት ውጤት ናቸው። ይህ ችግር ስር ሰዶ እያለ ህልውናችንን እየተፈታተነ፤ ከአምስቱ ኢትዮጵያዊ አንዱ የድርቅ ሰለባ እየሆነ፣ ሀገራችን የረሀብና የድህነት ምሳሌ እየሆነች፣ ክብራችንና ኩራታችን እንዳፈራችን በየጊዜው እየተሸረሸረ መሆኑ እየታየ ነው። በመሆኑም መፍትሄው ምንድነው? ምን ብናደርግ ይሻላል?

ከረሀብና ከድርቅ አዙሪት ለመውጣት ዋነኛውና መሰረታዊው መፍትሄ የተፈጥሮ አካባቢያችንን ማልማት መሆኑ የታወቀ ሲሆን ለዚህ ደግሞ የተፈጥሮ ጥበቃና እንክብካቤን የሚያስፈጽሙ ጠንካራ ተቋሞች ማዘጋጀት፣ ያሉትም ይበልጥ የሚጠናከሩበትን መንገድ ማመቻቸት፣ እንዲሁም ህብረተሰቡ የሚሳተፍበትንና በባለቤትነት አካባቢውን የሚንከባከብበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር እንደሚያሻ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ያካሄዱት ጥናት ያስረዳል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተመሰረተው በግብርና በመሆኑ ኢትዮጵያ በመሬትና በውሀ እንዲሁም በአየር ንብረት ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ጥገኛ ለመሆን ተገዳለች። የኢትዮጵያ ደህንነት የሚመሰረተው በአየር፣ በውሀ፣ በመሬት፣ በእጽዋትና በአዝርእት እንዲሁም አጠቃላይ በሆነ የአካባቢ እንክብካቤና ደህንነት ላይ ነው።

በዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ ግብርናን አደጋ ላይ ለሚጥሉ ሁኔታዎች ማለትም በመሬት በውሀና በነፋስ መሸርሸር፣ መሬት በኬሚካሎች ከጥቅም ውጭ መሆን ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል።በየአመቱ ከ 150 ሺህ እስከ 200 ሺህ ሄክታር ደን ይጨፈጨፋል። በዚህ የተነሳ መሬቱ በውሀና በነፋስ ለመሸርሸር ይዳረጋል። ስለዚህም በየአመቱ 2 ቢሊዮን ቶን ለም አፈር ይሸረሸራል። በአፈር መሸርሸር የተነሳ መሬቱ ለምነቱን ስለሚያጣ ገበሬዎች በየአመቱ ከ 20 ሺህ እስከ 30 ሺህ ሄክታር የእርሻ መሬትን ማረሳቸውን ለማቆም ይገደዳሉ።

ቀድሞ በየ15 አመቱና በየ10 አመቱ ልዩነት ሲከሰት የነበረው ድርቅ አሁን በየ5 አመቱና ከዛም በታች መከሰት መጀመሩ አካባቢ ጉዳቱ መባባሱን የሚያሳይ ነው። የኢትዮጵያ የተፈጥሮ አካባቢ በረጅም ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እየተራቆተ ይገኛል። ሁኔታው አስቸኳይ እና አጣዳፊ እንዲሁም ወሳኝ እርምጃን ይፈልጋል። በአሁኑ ጊዜ ያለው የተፈጥሮ አካባቢ መራቆት አደገኛ ከምንለው በላይ ነው።

# ለኢትዮጵያ አካባቢ መጎዳትና መራቆት ዋና ዋና ችግሮች

| ተ.ቁ | ችግሮች | ውጤታቸው |
|---|---|---|
| 1 | ደንና ዱርን መመንጠር | • መሬት ለነፋስና ለውሀ መሸርሸር መጋለጥ<br>• የመሬት ምርታማነት መቀነስ<br>• የሚታረስ መሬት መመንመን<br>• የአርብቶ አደሩ የግጦሽ መሬት ማጣት<br>• የዱር እንስሳት መሰደድ |
| 2 | የመሬት ባለቤትነት ስሜት አለመኖር | • ገበሬዎች ስለወደፊቱ የመሬት ልማት ሳይሆን ባጭር ጊዜ ስለሚያገኙት ጥቅም ብቻ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። |
| 3 | የህዝብ ብዛት መጨመር | • በተራሮች፤በከፍታ ቦታዎች፤በቁርጥራጭ መሬቶች እንዲሁም የተፈጥሮ ደኖችን እየመነጠሩ የእርሻ ቦታ ማድረግ። |
| 4 | አካባቢን ያላገናዘቡ የመንግስትፖሊሲዎች | ▪ የሚወጡ ፖሊሲና ህጎች በአካባቢ ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ ከግንዛቤ አለማስገባት፤<br>▪ ፖሊሲዎች የህዝብ ቁጥርን፡መሬትን፡የቀንድ ከብትን፡ደንንናውሀን እንዲሁምየዱር አራዊትን፡የአየር መበከልንና የህይወት ስብጥርን ከግምት ውስጥ ካላስገቡ በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትላሉ። |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | ተደጋጋሚና ሰፊ የደን ቃጠሎ | • የዱር አራዊቶችና አእዋፍ መሰደድ<br>• የስብጥረ-ህይወት መጥፋት<br>• ለግጦሽ የሚሆኑ ስፍራዎች መመናመን |
| 6 | የሀገር በቀል ደን አለመትከል | • ከሀገር በቀል ዛፎች ይልቅ ቶሎ የሚደርሱ ዛፎችን መትከል::<br>• ለምሣሌ ባህር ዛፍ ቶሎ ከሚደርሱ ዛፎች አንዱ ሲሆን ስሩ ከመሬት በላይ ስለሚዘረጋ በበቀለበት አካባቢ ምንም ዕጽዋት አይጸድቅም::<br>• ሥሩ ውሀ ስለሚመጥመሬት ውስጥ ያለውን ማእድን ያራቁታል:: |
| 7 | ተገቢ ፖሊሲዎችና ተቋሞችአለመኖር ያሉትም ቢሆኑ ደካማ መሆን:: | ▪ ፖሊሲዎችን የሚከታተል የሚቆጣጠር የሚያስፈጽም ጠንካራ አካል አለመኖር::<br>▪ ለአካባቢ ተቋማት ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት፤በሰው ሀይል፤በበጀት፤በአደረጃጀት ደካማ መሆን::<br>▪ ተቋማት ቢኖሩም ሚናቸው ግልጽ አለመሆን:: |
| 8 | ውሀና አፈርን የመንከባከብ ልማድ ውሱን መሆን | • የመሬት መሸርሸርን ያፋጥናል:: |
| 9 | ተመሳሳይ ሰብል በተደጋጋሚ ጊዜ አንድ ቦታ ላይ መዝራት | • የመሬትን ለምነት ያሳጣል:: |
| 10 | ፍግንና የመሳሰሉ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች በብዛት አለመጠቀም | • የመሬትን ለምነት ይቀንሳል:: |
| 11 | አካባቢን በተመለከተ ዝርዝር ፖሊሲ አለመኖር | • የደን ፖሊሲ<br>• የአፈርና የውሀ ጥበቃ ፖሊሲ<br>• የዱር አራዊት ጥበቃ ፖሊሲ<br>• የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ |

## የተሳሳተ የአካባቢ ፖሊሲ-ግጭት-የአካባቢ መራቆት

ባለፉት መንግስታት የተፈጥሮ አካባቢን በተመለከተ ብዙ ፖሊሲዎች ቢወጡምና ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ቢደረጉም ዘላቂ ውጤት ለማምጣት አልተቻለም:: ለዚህ እንደዋነኛነት የሚጠቀሰው አካባቢን በተመለከተ የተደረጉ ልማቶች ህብረተሰቡን ባለማሳተፉና የባለቤትነትም ስሜት ለማሳደር ባለመቻሉ ነው:: ይህም የተረጋገጠው መንግስት ያሰማቸውን ደኖች፤ የተከለሉ ብሔራዊ ፓርኮችንና መሰል ልማቶችን የመንግስት ለውጥ በሚደረግበትና የሚያጋጥሙ አለመረጋጋቶችን በመጠቀም ህዝቡ 'ሆ' ብሎ ለማውደም መነሳቱ ነው::

መንግስት የተፈጥሮ አካባቢ ልማትን በተመለከተ የተሳሳተ ፖሊሲ ፈጽሟል ተብሎ በህዝቡ ዘንድ ከታመነ አጋጣሚን በመጠበቅ ውድመት ከማድረስ ወደ ኋዋላ እንደማይባል ካለፉት ክስተቶች መማር ይቻላል::

የኢትዮጵያ ህዝብ ባብዛኛው በግብርና ስለሚተዳደር የአካባቢ መራቆት ወደ ኢኮኖሚ ችግር ሊያመራ ስለሚችል አልፎ አልፎም ቢሆን በአካባቢ መጎዳት ሳቢያ ግጭቶች ሲፈጠሩ ይታያል:: ለምሳሌ በአርብቶ አደሮች እና በገበሬዎች መካከል የሚፈጠረው የተለመደ ግጭት ገበሬዎች የእርሻ መሬትን ለማስፋፋት የግጦሽ ቦታን ሲመነጥሩ ነው::

በደቡብ ኢትዮጵያ በቦረና አርብቶ አደሮችና በኮንሶ ገበሬዎች መካከል፤ በሸዋሮቢት አካባቢ በአማራ ገበሬዎችና በአፋር አርብቶ አደሮች፤ በአፍደር አካባቢ በኦሮሞ ገበሬዎችና በሱማሌ አርብቶ አደሮች፤ እንዲሁም በአፋር አካባቢ ተስፋፍቶ የነበረው የመንግስት የእርሻ መሬት በአፋሮች ዘንድ ቂም ፈጥሮ በምርት ወቅት ተደጋጋሚ ግጭትና ትንኮሳ ደርሷል::

## የተፈጥሮ አካባቢን ለመንከባከብ ያሉ ችግሮች

- በመሬት አጠቃቀም፤በደን፤በዱርአራዊት፤በሰብል፤በከብቶችና በመሳሰሉት አጠቃቀም እንክብካቤ ላይ በቂ ፖሊሲዎች፤ህጎች፤ስልቶችና የተግባር መርሆዎች ፈጽሞ አለመኖር:
- ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፉ ሊደርስ የሚችለውን የአካባቢ ጉዳት በየጊዜው እየገመገመ ሪፖርት የሚያደርግ አካል አለመኖር::
- ለደን ልማት ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት ፤ የደን ልማት በግብርና ሚኒስቴር ስር እንደዋዛ በአነስተኛ ደረጃ ብቻ መዋቀሩን እንደምሳሌ ማየት ይቻላል::
- በአካባቢ ላይ የሚደረገው ጥናት ዝቅተኛ ትኩረት መሆን፤ብሔራዊ የአካባቢ ምርምር ተቋም የዶክሜንት ማዕከል ወይም ተቋም አለመኖር::
- በዚህ የተነሣ በአካባቢ ላይ የሚደረገው ጥናት የተበታተነ-ቅደም ተከተል የሌለው- ለከፍተኛ ወጪ የሚዳርግ መሆን
- የቴክኖሎጂ እጥረት

- ሐገር በቀል ልማዳዊና ባህላዊ እውቀቶችን ቸል ማለት::
- በአካባቢ ላይ በቂ ስልጠና ያላቸው ባለሙያዎች አለመኖር::
- በቂ የዕቅድ፣የአስተዳደር የክትትል የግምገማ ዘዴ አለመኖር::
- የአካባቢን ኢኮኖሚ ከግንዛቤ አለማስገባት
- አካባቢን በተመለከተ ህዝቡ በቂ ትምህርት አለማግኘቱ::
- የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር በየ ሀያ ሦስት አመቱ በእጥፍ ይጨምራል::
- ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ህዝብ ውስጥ ግማሹ ከ15 አመት በታች ነው::
- ከበቂ በላይ በታረሱና እንክብካቤ በሌላቸው የእርሻ መሬቶች ላይ የህዝብ ብዛት እየጨመረና መጨናነቅ እየተፈጠረ ነው::
- መሬቱ ለምነቱን ጨርሶ በተሸረሸረበት በዚህ ቦታ ብዙ ህዝብ በመስፈሩ ለምግብ እርዳታ ጥገኝነት ተጋልጠናል::

## ማጠቃለያ

የተራቆተውንና የተጎዳውን የኢትዮጵያ መሬት እንደገና እንዲለማ ምን ቢደረግ ይሻላል? ለሚለው ፈታኝ ጥያቄ እንደ ጊዜዮን አስፋው ያሉ በዘርፉ ከፍተኛ እውቀትና ልምድ ያላቸው የአካባቢ ተመራማሪዎች ዘመቻን ጨምሮ ስር ነቀል የሆነ የፖሊሲ እርምጃ ቢወሰድ መፍትሔ ይሆናል ብለው ያምናሉ::

የአካባቢ መልሶ ማለምለም ዘመቻ በሀገሪቱ ያሉ ትምህርት ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ወታደራዊ ማሰልጠኛዎች በሙሉ ካሉበት ቢያንስ ከ10 እስከ 15 ኪሎ ሜትር ዙሪያ-ገብ ድረስ ያሉ ቦታዎችን በደን የማልበስና መሬት እንዳይሸረሸር የመከላከል ስራ እንደ ብሔራዊ ግዴታ የሚሰሩበት ሁኔታ እንዲመቻች ሀሳብ ያቀርባሉ::

በዘመቻው የሐይማኖት ተቋማት ቢያንስ የሚያመልኩበትን አካባቢ እንዲንከባከቡና የሀይማኖት አባቶችና ምዕመናን ስለአካባቢ ልማት ግንዛቤ አግኝተው በዘመቻው አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ከፍተኛ ቅስቀሳ ቢያደርጉ::

አካባቢን መልሶ ለማለምለም በሚደረገው ዘመቻ መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ለዘመቻው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን በማቅረብ፣ ቴክኒካዊ ምክሮችን በመለገስና ባለሙያዎችን በማስማራት መተባበር::

የተሸረሸሩና ለእርሻ የማይሆኑ ቦታዎችን ለደን ልማት እና ለመዝናኛ ሥፍራዎች እንዲያገለግሉ የክልል መንግስታትና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ከቢሮክራሲ እና ከክፍያ ነጻ አድርገው ቢያቀርቡላቸው:: የደን ልማቱ እየጠፉና እየተመናመኑ ላሉት ሀገር በቀል ደኖች ማለትም ለጥቁር እንጨት፣ ዋንዛ፣ ቀረሮ፣የሀበሻ ጽድ፣ ኮሶ፣ ዝግባ፣ ወይራ፣ ኮርችና የመሳሰሉት ቅድሚያና ትኩረት ቢሰጥ::

አካባቢን መልሶ ለማለምለም በሚደረገው ዘመቻ በዋና ባለቤትነት የሚታቀደው፣የሚዘጋጀውና የሚፈጸመው በወረዳ ደረጃ ቢሆን ይህ ዘመቻ ውጤታማና ዘለቄታ ያለው ለውጥ ሊያመጣ ይችላል::

ከዘመቻ ባሻገር ተገቢ የሆኑ መስሪያ ቤቶችንና እርስ በርስ የሚገናኙ ፖሊሲዎችን የሚያካትት የአካባቢ ፖሊሲና ህግ በፍጥነት ማውጣት:: የሚወጣው ፖሊሲና ህግ ያለ ችግር ተግባራዊ የሚሆንበትንና አካባቢ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ከግንዛቤ በማስገባት ዝርዝር መመሪያዎችን በማዘጋጀት ዘለቄታ ያለው የተፈጥሮ አመራርን ማረጋገጥ::

በፌደራሉም ሆነ በክልል መንግስታት የስፈራ ፕሮግራም ሲዘጋጅ በአካባቢ ላይ ያለውን ተጽእኖ በሚገባ በመገምገምና በማጥናት ያለፈውን ስህተት ላለመድገም መጣር ሊታሰብበት የሚገባ ዋና ጉዳይ ነው::

የሚመለከታቸውን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ተቋሞችን፣የሙያ ማህበራትንና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያካትት፣የልማት አጋሮችንና አስፈላጊ የአለም አቀፍ ማህበረሰቦችን በማሰባሰብ ዘለቄታ ያለው የተፈጥሮ አካባቢ አመራርን በማዘጋጀት ለተግባራዊነቱም ተገቢ ተቋም መፍጠር::

ፖሊሲዎችን፣ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችንና ዝርዝር መርሀ ግብሮችን ለመንደፍና ለማዘጋጀት እንዲሁም ለማቀናጀት ጉልህ ሚና የሚኖረው የአካባቢ የምርምርና የዶክመንት ተቋም ወይም ማዕከል አስፈላጊ በሆነበት ስፍራ ሁሉ ጊዜ ሳይሰጠው ማቋቋም::

አካባቢን ለሙሥራትና በዚሁ ላይ ለመመሪመር በሚደረግ ማንኛውም ጥረት ውስጥ ማህበረሰባዊና ባህላዊ ጉዳዮችን እንዲሁም ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ማካተት::

ሥርአተ ትምህርቱም ሆነ የትምህርት መጽሐፎች የአካባቢ እንክብካቤ ትምህርትን በጥራትና በብቃት መያዛቸውን ማረጋገጥ::

አስፈላጊ በሆነበት ሁሉ አካባቢን የተመለከተ ጠንካራ የፕላን፣የቁጥጥር የግምገማ ዘዴ በማዘጋጀት ::የኢንደስትሪ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት በአካባቢ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት የረጅም ጊዜ ተፅዕኖና ጉዳት የሚገመገምበትን ዘዴና ስርዐት ማዘጋጀት ያሉትንም ማጠናከር::

አካባቢ ከህልውናችን ጋር በቀጥታ የተቆራኘ መሆኑን በመረዳት ለአካባቢ እንክብካቤና ምርምር በተቻለ መጠን በቂ የሰው ሃይል፣የገንዘብና የማቲሪያል ድጋፍ ማድረግ::

በአካባቢ መራቆት ከወንዶች ይልቅ ሴቶች የበለጠ ተጠቂ መሆናቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ ::በመሆኑም
በአካባቢ ፖሊሲ የሴቶችን ተሳትፎ ማጉላት::ወጣቶች በአካባቢ ልማት በዘላቂ መንገድ የሚሳተፉበትን መንገድ ማመቻቸት::

የየአካባቢው ነዋሪዎች የአካባቢ ልማትን በዋና ባለቤትነት እንዲንከባከቡ፣ እንዲቆጣጠሩ፣ የኔነት መንፈስ ሥር እንዲሰድ የሚረዱ ፖሊሲዎችን ማውጣትና ያለ ችግር ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት:: ተግባራዊነታቸውንም በየጊዜው በመገምገም ማረጋገጥ::

አካባቢን ከመንከባከብ ጋር ለተያያዙና ለሀገር በቀል የደን ልማቶች ኢንቨስትመንት ቅድሚያ መስጠት ማበረታታት ሌሎችም መዋዕለ-ነዋይ እንዲያፈሱ መቀስቀስ::

ተጀምረው በእንጥልጥል ለቀሩ የአካባቢ ፕሮጀክቶች ለምሳሌ እንደ አልዌሮና ጣና በለስ የመሳሰሉ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ በመስጠት የአካባቢ ልማትን ማጠናከር::

የኢትዮጵያ መሬት ለዘመናት ትውልድን ሲመግብ እንደቆየው ሊቀጥል የማይችልበት ደረጃ በመድረሱና ህዝቦቹዋ ህይወታቸውን ለማቆየት በእርዳታ እህል ላይ ጥገኝነታቸው በየጊዜው እየጨመረ በመምጣቱ
ፈጣንና ወሳኝ የፖሊሲ እርምጃ ያስፈልጋል::

ይህ ጽሁፍ "የሲቪል ማህረሰብና የአካባቢ ፖሊሲ ውይይት" በሚል ዋና ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ:-አካባቢና የአካባቢ ለውጥ በኢትዮጵያ፣አካባቢ-ድህነት-ጾታ፣የአካባቢ ግጭት፣የኢኮኖሚ ልማትና በአካባቢ ላይ የሚደርስ ተጽዕኖ፣መንግስትና የአካባቢ ፖሊሲ.....ወዘተ የሚሉ 18 ጥናታዊ ጽሁፎች በምሁራኖች፣መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚሰሩ ኤክስፐርቶችና ባለሙያዎች ተዘጋጅተ ከቀረበውና በውይይት ዳብሮ በማህበራዊ ጥናት መድረክ ከታተመው የተቀነጨበ ነው::የበለጠ መረጃ ከፈለጉ ወይንም ጥናታዊ ጽሑፎቹን ለማንበብ በሚከተለው አድራሻ ይጠይቁ::

መጋቢት 1996

ማህበራዊ ጥናት መድረክ:-
የመልዕክ ሳጥን ቁጥር 25864 ኮድ1000፣አዲስ አበባ
ስልክ ቁጥር:-57-29-90/57-29-91
ኢ -ሜል :-fss@telecom.net.et
ድረ-ገጽ www.fssethiopia.org